# ቂም በቀል ወይስ ፍትህ ?

በአለም አቀፉ መድረክ የተባበሩት መንግስታትን አርማ አጥልቆ በኮንጎ ለተሰለፈው ሰራዊት ከፍተኛ የሎጅስቲክ አቅርቦት ሥራን ያከናውን የነበረው የኢትዮጵያ አየር ኃይል ወደር ላልተገኘለት ጀግንነቱና ለዓለም ሰላም መከበር አስተዋፅኦው የዘመኑ ድንቅ አየር ኃይል በመባል ወገንን አኩርቷል ።

በጐረቤት ሶማልያ ለደረሰው የውሃ መጥለቅለቅ አደጋም በአስደናቂ ፍጥነት ደርሶ ከህይወት ማዳኑ ተግባር ጐን ለጐን ምግብና መድሃኒት ለተጐጂው በማቅረብ ለአካባቢው ህዝቦች ጭምር አለኝታነቱን አስመስክሯል ።

ለዘመናት አገራችንን ኢላማ አድርጐ የያዛትን የአካባቢያዊ ሰላም ማጣት ሥጋት ጋር ተያይዞ በተደጋጋሚ በእብሪት የተቃጣብንን ወረራ በግምባር ቀደምትነት በመሰለፍ የአየር ክልላችንን ከማስከበር አልፎ በምድር ለተሰለፈው የወገን ሰራዊት የቅርብ ረዳት ሲሆን ለጠላቶቻችን ደግሞ የማይፈታ ቅዠት በመሆን ዛሬ ድረስ አለ ።

በቅርቡም የአሁኑ ገዢ ፓርቲ ከኤርትራ ጋር በአደረገው ግጭት በመጨረሻው ጦርነት ለቀድሞው የአየር ኃይል ሰራዊት ጥሪ በማቅረቡ ለአገሩ ሁሌ ቀናኢ የሆነው የአየር ኃይል አባላት በሰጡት ፈጣን ምላሽ የተመረጡ ወታደራዊ ኢላማዎችን በብቃት በመደምሰስ በአገር ላይ ሊደርስ የነበረውን ውርደት በአጭር ቀናት ሊቀለብሰው እንደቻለ የምናስታውሰው ነው ።

ይሁን እንጂ የአየር ኃይሉን የሃገርና የወገን አለኝታነት ፤ በተጨማሪም ኢትዮጵያዊ ጀግንነትን ለማኮስመንና ለማጥፋት በስመ ጥሩው የአየር ኃይል በራሪዎች ላይ የብቀላ ክስ በመመስረት እነሆ እንደተራ ነፍሰ ገዳይ ለሞትና ለእድሜ ልክ እስራት ፍርድ በቅተዋል ።

የአሁኑ ገዢ ፓርቲ በተቃዋሚነት ዘመኑ አለም አቀፋዊ የጦርነት ህግን በመተላለፍ ሰላማዊ ሰዎችን በከለላነት (Human shield) በመጠቀም ሆን ብሎ ካሜራውን አዘጋጅቶ ታንክና መድፉን ወደ ሰላማዊ ሰዎች ወረዳ ይዞ በመግባት በጊዜው በስልጣን ላይ ለነበረውም መንግስት የተሳሳተ መረጃ እንዲደርሰው በማድረግ የአቀናበረውን ፊልም በአለም ላይ እንደቸበቸበና የአለምንም ህዝበ እንዳወናበደበት ከቀድሞው የህውሃት መስራች መሪዎች የተጋለጠ ደባ እንደሆነ የአደባባይ ሚስጢር በሆነበት በአሁኑ ሰዓት ለ18 አመታት ያለ አንዳች ፍርድ በማጎሪያው እንዲማቅቁ ያደረጋቸውን እንቁ የአገር ሃብት በራሪዎችን፤በተጨማሪም ለሃገራቸው የአየር ክልል መከበር ህይወታቸውን ካጡ ከ20 አመታት በላይ ያስቆጠሩትን ሰማዕታትን በአፅማቸው ላይ የሞት ፍርድ መፍረዱ መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ያሳዘነ ጉዳይ ነው ።

በሂሮሺማና ናጋሳኪ የአየር ድብደባ ተዋናይ የነበሩት በራሪዎች እንደማንኛውም ወታደራዊ ግዳጅ ፈፃሚ ለፈፀሙት ጀብዱ እስከመጨረሻው በብሄራዊ ጀግንነታቸው

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሲታወቁ ፤ የኢትዮጵያ አየር ኃይል በራሪዎች ሃብታቸውንና ኑሮዋቸውን ፤ በተጨማሪም መላውን ጊዜያቸውን አገራቸውንና ህዝባቸውን ከውርደት ለማዳን ደማቸውን በማፍሰሳቸው ሞትና እድሜ ልክ ፍርድ መፈረዱ ታሪክ ሊሽረው የማይችል የአገር ክህደት ከመሆኑም በላይ የአየር ኃይሉ አዛዦች እነ ጀነራል ፋንታ በላይና ጀነራል አመሃ ደስታ ለአገሪቱ ሰላምና ደህንነት ያደረጉት መስዋዕትነት ላይ መቀለድ ሲሆን በመጨረሻዋም እለት ጀነራል አመሃ ደስታ የኢትዮጵያን ባንዲራ ለብሰው በገዛ እጃቸው መስዋዕት መሆናቸው ለአገራቸው አንድነት እንደነበረ እያስታወስን፤በአሁኑ ሰዓት በቀድሞው የአየር ኃይል ጀግኖች በራሪዎች ላይ የተፈረደውን የክህደት ፍርድ አጥብቀን የምንቃወም መሆናችንን በቁርጠኝነት እያሳወቅን፤ መላው ያገራችን ሰላም ወዳድ ህዝብና አለም አቀፉ ህብረተሰብ ከጐናችን እንደሚቆም እምነታችን የፀና ነው ።

ከቀድሞው የኢትዮጵያ የአየር ኃይል ማህበር
በሰሜን አሜሪካና በመላው ዓለም ።

አፕሪል - 2008
ዋሺንግተን ዲሲ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com